ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ቅፅ 38 ቁጥር 4 ግንቦት 2005 ዓ.ም

# ግንቦት እንደገና

“ አገመገመ ሰኔና ግንቦት፥
ለኢትዮጵያ ትንሳዔ ለወያኔ ሞት !”

የኢትዮጵያ ገበሬ እንጉርጉሮ

አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ የዓመት ወሮች ፥ የየራሳቸው የታሪክ ፥ የባኅልና የሃይማኖት አሸራዎችን እያስመዘገቡ አልፈዋል። ወራት ሲፈራረቁም የሚያመጧቸውና ትተዋቸው የሚያልፉት አያሌ አጋጣሚዎችና ትውስቶች አሉ ። በወረርሽኝ በሽታ መንስዔ የብዙ ዜጋ ሕይወት የተቀሰፈው በህዳር ወር ስለነበረ ፥ ወረርሽኙ የህዳር በሽታ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ቆይቷል። በመሆኑም ፥ታሪክ ፥ወሩን የሚያስታውሰው ኅዳር በሽታ እያለ ነበር፥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድርስ ! ይህ የኅዳር በሽታ በታሪክ፥ ለብዙ ጊዜ ከሕዝብ ኅሌና ሊፋቅ ያለቻለው ፥ብዛት ካለውና አሰቃቂ ከሆነው የሕዝብ እልቂት የተነሳ፥የሞተውን የሚቀብር በሕይወት የተረፈ አንድም ሰው ስለአልነበረ ነው ። በዚህ ምክንያት፥ሬሳው ሁሉ ቀባሪ አጥቶ፥ የዱር አራዊትና የሰማይ አሞራ ሲሳይ ሆኖ በመቅረቱ ነው ተብሎ ይነገራል።

ሌሎቹም ወራት እንደዚሁ፥በታሪክ ደስታም ይሁን ሀዘን ፤ መከራም ይሁን ሀሴት ፤ ድልም ይሁን ችንፈት፥ውርደትም ይሁን ኩራት፥ረሀብም ይሁን ጥጋብ ወዘተ አፈራርቀው አልፈዋል። የሁሉንም አሸራ፥ ታሪክ በየፈርጁ ስለመዘገበው፥ የሀገራችን ታሪክ ሆኖ ቆይቷል።

የሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት (1928 ) ዓመተ- ምህረቱ ግንቦት፥ ወራሪው የፋሽስቱ ኢጣሊያ ጦር አዲስ አበባ የገባበትና የዓምስት ዓመት የቅኝ ግዛት ሙከራ የጀመረበት ወር ነበር። ዋናውን ከተማ አዲስ አበባን፥ ከሙሶሊኒ ወራሪ ጦር ለመከላከል ሲባል ያለቀው አርበኛ ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት በዚሁ በግንቦት ወር እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል ። ወረሃ ግንቦት፥ የየራሳቸው የሆኑ የታሪክ አሸራዎችን አስቀምጦ ሄዷል ። በታሪክ አጋጣሚም ይሁን በሌላ ምክንያት፥የግንቦት ወር የቅርብ ጊዜ ትዝታው የብዙ ንፁሃን ዜጎች ደም በግፍ የፈሰሰበት አጋጣሚዎቹን በመሪር ሀዘን እንድናስታውስ ያደርገናል ።

የኢትዮጵያ ሠራተኞች፥ የ1969 ግንቦት አንድ ቀን፥ በማኅበራቸው በኢትዮጵያ ሠራተኞች ኮንፌዴሬሽን ( Confederation Of The Ethiopian Labor Union {CELU})
የተጠራውን በዓላቸውን ለማክበር ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣታቸው፥ በሽ የሚቆጠሩት ያለ

ርጎራጌ በመትረየስ ተረሽነዋል ። ሰልፉን ለማየት የወጡ ዜጎች ሁሉ ፥ የጥይት ራት ሆነው ወድቀዋል ። የብዙ ቤተሰብ አባላት የሀዘን ከል ለብሰው ቀርተዋል ። በዚህ ዕለት ፋሽስታዊውን የደርግ አገዛዝ ለመቃወም ሰለፍ የወጡት የኢሕአፓ ወጣቶችም ክቡር ደማቸው የአዲስ አበባን ከተማ አጥለቅልቆት ነበር ። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር አባላትና ደጋፊዎች፥ በዚህ የሠራተኞችን ቀን በዓል ለማክበር በተጠራው ሰላማዊ ሰለፍ በመገኘታቸው ምክንያት ብቻ መረሸናቸውን ዛሬም ቢሆን፥ ይህን ቀን ኢትዮጵያውያን የሚያስታውሱት ከመሪር ሀዘን በመነጨ የልብ ውጋትና የአዕምሮ ስብራት ነው ።

ኢሕአፓም ይህንን ሀዘን የሚዘክረው፥ በዚያን ወቅት የተጨፈጨፉትን አባላቱንና ዜጋዎቹን በማስታወስ ይሆናል። ጥቃትና በደል መታወስ ያለበት ፥ የመከራን ታሪክ ለመዘከርና፥ ወደ ፊትም ያ ድርጊት እንዳይደገም ሁሉም ዜጋ እንዲያስብበት እንጅ ፥ የበቀልን ቁጭት ለመወጣት መሆን እንደማይገባው እናምናለን ። በቀል፥ በቀልን ስለሚያስከትል፥ የግድ በአንድ ወቅትና በአንድ ትውልድ መቆም አለበት ! ይህን መሠረታዊ ቁም-ነገር ዛሬ ፥ በሁሉም ዜጋ አዕምሮ ሊጉላላና ሊታስብበት ይገባል። መጭው ትውልድም፥ በቂምና በበቀል አዙሪት ውስጥ እንዳይገባ ፥ ይህ የወቅቱ ትውልድ ኃላፊነቱን ማውርድ ይጠበቅበታል ። ሌላው ቢቀር፥ የሀገራችን ተተኪ ትውልድ ፥ በቂም - በቀል አዙሪት ውስጥ ኅብቶ እንዳይሽከረከር ዛሬውን ብልኀነት ሊገኝለት ይገባል ።

ከአርባ ዓመት በፊት የዚያን ሁሉ ደም መፍሰስንና የብዙ ሰራተኞችንም ሕይወት የጠየቀው መሥዋዕት ከተከፈለም በኋላ ፥ ዛሬም በወያኔው ዘረኛ ሥርዓት፥ የኢትዮጵያ ሠራተኞች፥ መብታቸው፥ ጥቅማቸውና የድርጅት ነፃነታቸው አልተከበረላቸውም ። በነፃ የመደራጀት መብታቸውም የሚታሰብ አልሆነም ። ሰራተኞች በማኅበራቸው ሕግና ደንብ መሠረት የመረጧቸውን ዕውነተኛ ወኪሎችና መሪዎችን አስሮ ፥ ገድሎና አሰድዶና ማኅበራቸውንም አፍርሶ፥ በዘርና ቋንቋ ላይ የመሰረተውን የራሱን አምሳያ ጠፍጠፎ ፥ የሠራተኛውን ኅብረተሰብ እንቅስቃሴ ይቆጣጠረዋል ። ሠራተኛው በነፃ የመደራጅትና የመንቀሳቀስ መብቱ በህግ አረጋግጦ የመስራት ዕድሉ ዋስትና ኖሮት፥መብቱን እያሰከበረ ጥቅሙን እያስጠበቀ መኖር አልተቻለውም ።ይህ ደግሞ ከቶ የሚያስገርም አይደለም ።ምክንያቱም ፥ ጠቅላላ የሀገሬው ዜጋ በሞላ በአምባገነን ሥርዓት ስር ስለወደቀ ፥የኢትዮጵያ ሠራተኛው ኅብረተሰብ የተለየ የዴሞክራሲ መብት ይኖረዋል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው ።

የአንድ አምባገነን ሥርዓት፥ ማንነት፥ባኅርይም ሆነ ተግባር ሊታይና ሊገመገም የሚገባው ፥ ያ ሥርዓት ፥ በሀገሪቱና በዜጎቿ ላይ ከሚፈፅመው ብሔራዊ ወንጀልና ከሚያደርሰው ሀገራዊ ጉዳት አኳያ ነው ። የወቅቱ ወያኔዎችም ይህንን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ ። ለሚፈፅሙት ወንጀልና ለሚያደርጉት የሕዝብ በደልና የሀገር ጥፋት ሙሉ ተጠያቂዎች ናቸው ። በመሆኑም ፥ የነኝህን ቡድኖች ፥ ዘረኛ ሥርዓት ፥ ከስረ - መሠረቱ ጥሎ ፥ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት፥ አጣዳፊና የሕዝብ ትግል ፥ቀዳማይ አጀንዳ መሆን አለበት ። ምክንያቱም፤ በአምባገነን ሥርዓት ለሚሰቃይ ዜጋ ፥ይህን ሥርዓት ከነአካቴው ከማስወገድ በቀር፥ ሌላ መፍተሄ ስለማይኖር ነው ።

በ1981 ዓም የመጣው ግንቦትም፥ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለማስወገድ የተሞከረው መፈንቀለ-ሥልጣን በመክሸፉ ፥ ሙከራውን ጠንስሳቸኋል የተባሉ ምርጥ የሀገሪቱ የጦር መሪዎች ደም በከንቱ እንዲፈስስ ሆኗል። ይህኛው ግንቦት በተለይ የሚታወቀው፥ ሀገሪቱን ከውጭ ጠላት ለመከላከል የሚችሉ ጀግኖችና ሀገር ወዳድ ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎች በግፍ የተረሸኑበት ወር በመሆኑ ነው ። የእነኝህ የሀገሪቱ ምርጥ ጀኔራል መኮንኖች በገፍ

መጨፈጨፍ÷ ወያኔና ሻአቢያ “ ላሜ ወለደች” ብለው÷ የደስታ ጮቤ ረግጠዋል ። ኀይላ ጨፍረዋል ። አዲስ አበባና አስመራ ሰተት ብለው ለመግባት በሩ ተከፍቶላቸዋል ። ጀኔራል መኮንኖቹን ያስጨፈጨፈው ግለሰብም ግን ÷ ሀገራችንንና ሕዝቧን አጋልጦ ሸሽቶ አምልጧል። እስከ ዛሬም ድርስ ለፍርድ ሳይቀርብ እንደልቡ ይኖራል። ይህ የግንቦት ወር÷ በተለይ በሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ጥሎት የኼደው ጥቁር ነጥብ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። የሀገሪቱን የመከላከያ ሠራዊት÷ የንፁሃኑን ደም በግፍ ካፈሰሱ አምባገነንን መሪዎች በመለየት÷ ወንጀለኞቹን ለፍርድ ማቅርብ እንጅ÷ ሌሎቹን የጦር መሪዎችንና የሠራዊቱን አዛዥ መኮነንኖች መጨፈጨፍ÷ጉዳቱ የሀገር ነው ። ይህንን ያለተረዳው ደርግ÷ በሀገርና በሕዝብ ዘንድ በቀላሉ ያልተጠገነ በደል ፈፅሞ አልፏል ።

የአስራ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አንድ ( 1983) ዓም ዓመተ- ምህረቱ ግንቦት ወር ደግሞ ÷ የራሱን ጦስና መከራ÷ የሀገር ጥፋትንና የሕዝብ ዕልቂትን÷ እንዲሁም የታሪክ ውርደትንና ሀፍረትን አዝሎ የመጣ በመሆኑ ÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃና ሀዘን ዕጥፍ - ድርብ አድርጎታል ። የኢትዮጵያን መዳከምና የሕዝቧን መከፋፈልም አጥብቀው ሲመኙላት የኖሩ የውጭ ጠላቶች÷ ወያኔን ረድተውና መርተው አዲስ አበባ ሰተት ብሎ እንዲገባ በማድረግ÷ ሀገሪቱን ለመቆጣጠር በቅተዋል ። የወያኔን መሪዎች እንደ ትሮጃን ፈረስ እየተጠቀሙ ÷ የሀገሪቱን ዳር-ድንበር ብቻ ሳይሆን ÷ ውስጠ-ምሥጢሯን ሳይቀር የማወቅ ዕድል አግኝተዋል ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን የነፃነት ታሪክ÷ ታይቶና ተከስቶ የማይታወቅ ውርደት ነው ። የወቅቱ ትውልድ÷ ዛሬ በእርሱ ዘመን የሚፈፀመውን ብሄራዊ ውርደት እያየ÷ ከመታገል የተሻለ ምርጫ እንደሌለው ይገነዘባል ። የወያኔ መሪዎች በሀገራችን ላይ የሚፈፀሙትን ሀገራዊ ወንጀልም ሆነ÷ የሕዝብ በደልና ጥፋት ቢያደርጉ ÷ አያስገርምም ። ይህንን ለማለት በቂ ምክንያት አለ ።

አንድ የወያኔ መስራች አመራር አባል የነበረ ግለሰብ በቅርቡ ጽፎ ይፋ ባደረገው ሰነድ ላይ እንደገለፀው ÷አብዛኛዎቹ የወያኔ መስራቾች÷ አባቶቻቸው የኢጣሊያ ባንዳዎች እንደነበሩ መዝግቧል ።ታዲያ ከወላጆቻቸው የወረሱትን ከመፈፀም ሌላ ምን ይጠበቅባቸዋል ? የባንዳ ባኅርይና ተግባር ቀጥታ ትርጉሙ ÷ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም አሳልፎ ለባዕዳን መሸጥ ስለሆነ÷ አፍለኛ ጥቅምን ÷ በሀገረና በሕዝብ ዘላቂ ጥቅም መለወጥ ለወያኔዎቹ ትርጉም አይሰጣቸውም ። የመንግሥት ሥልጣን እንዲይዙ ሁለንተናዊ ትብብር ያደረጉላቸው ባዕዳን ኃይሎች ÷ በሥልጣን እንዲቆዩላቸው ስለሚፈልጉ ÷ ማንኛውንም ርዳታና ስጦታ ያደርጉላቸዋል ። ይህ ሁለንተናዊ ርዳታም ÷ የገንዘብ ÷ የመሳሪያና የማቴርያል ÷ የዲፕሎማቲክና የፖለቲካ÷ የኢንተሊጀንስና ሥልጠናንም ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ።

በአሁኑ ጊዜ የወያኔ መሪዎች÷ ከምዕራባውያን መንግሥታትና ከገንዘብ አበዳሪ ተቋማት÷ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ያገኛሉ። የዚህ ገንዘብ ርዳታ መጠን÷ በአፍሪካ አህጉር ከግብፅ ቀጥሎ ÷ ኢትዮጵያን በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጧታል ። ይህ ሁሉ ጎልቁ- መሳፍርት ገንዘብ የሚውለው ግን ለሀገር ልማትና ለሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ÷ ተጠቃሚዎቹ የወያኔ መሪዎችና ወገኖቻቸው ብቻ ናቸው። የሚጠቀሙበትን እየተጠቀሙ ቀሪውን ወደ ውጭ ስለሚያሸሹት ÷ የውጭ ሀገር ባንኮች ሁሉ ተንበሽብሸዋል ። ምዕራባወያኑም÷ ገንዘቡ የት የት እንደሚውል ለመቆጣጠር የሚያስስባቸው ጉዳይ የለቻውም ። የእነርሱ ተቀዳሚ አጀንዳ ÷ የወያኔ በሥልጣን ተደላድሎ የመቆየቱ ጉዳይ እንጅ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ይሁን ÷ የሀገሪቱ ዕድገትና ልማት አይደለም ። ይሆናልም ተብሎ አይጠበቅም ።

ለውጭ ባዕዳን÷ በኢትዮጲያ የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን÷ የሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ÷ መልካም አስተዳደር መዘርጋት ÷ የነፃ ፕሬስ መከበር ÷ የተቃዋሚ ድርጅቶች በነፃ የመንስቀሳቀስ ወዘተ... ጉዳያቸው አይደለም ። ይህ እውነታ ደግሞ ተብሎ ተብሎ ÷

ያበቃለት ጉዳይ ነው ። ይህንን ራሱን እንደ አዲስ ክስተት አድርጎ ማውሳቱ÷ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ ፋይዳ አያመጣም ። የወያኔ መሪዎችን ማንነት እያነሱ እየጣሉ መብተክተክ እንዲሁ ለትግሉ ሂደት አንድ ስንዝር አይጠቅምም ። ለአምባገነን ሥርዓትም የሚገባው ቋንቋ አይደለም ። የሚረዳበት ቋንቋ እንዲነገረው ከተፈለገ ÷ ዓብነቱ ሕዝባዊ አመፅ ብቻ ነው ። ይህ ሕዝባዊ አመፅ በቅርቡ ÷ በሌሎች ሀገራት አምባገነኖችን እንዳሰወገደ ÷ወያኔና ባዕዳን አለቆቹ በገሚገባ ይረዱታል ። በመሆኑም÷የሕዝብን ሁኔታም ይሁን የተቃወሚ ኃይሉን እንቅስቃሴ ለመከታተል ሲባል ÷ መጠነ ሰፊና ዘርፈ -ብዙ አውታር ያለው የኢንተለጀንስ እንቅስቃሴ በሀገራችን ውስጥ በመካሄድ ላይ የሚገኘው ። ማነኛውንም እንቅስቀሴ እየተከታተሉ መቆጣጠር÷ የመረጃ ተግባር ዓይነተኛ ዓላማ ስለሆነ ÷ ወያኔ ያለ ስጋት በሥልጣኑ እንዲሰነብት አድርጎታል ። የአራት መንግሥታት የመረጃ አውታሮች እንቅስቃሴዎች ለወያኔን ዘብ ቆመውለታል ። ወያኔዎቹም፦“ **ዕድሜ ለጡት አባቶቻቸን÷ ለብዙ ዘመን ያለስጋት በሥልጣን መቆየታችን አይቀርም** " ። ከሚል ቅዠት ደርሰዋል ። የዚህ ዓይነቱ ቅዠት ÷ የሕዘባዊ አመፅን ታሪካዊ ሃቅና ኃይል ካለመረዳት የሚመነጭ ከንቱነት ነው ። ሕዝባዊ አመፅ ሲያጥለቀልቅ ÷ የባዕዳን የመረጃ መረብ የቱኒዚያውን አምባገነን ቤን አሊንም ሆነ የግበፁን አምባገነን ሙባረክን አላዳነም ። እንዲያወም በቁርጡ ቀን “ **የአሙኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ** ” የሚባል ተረት ነው የሚከሰተው ። ወያኔዎች ይህነን ሀቅ ተቀበሉትም አለተቀበሉት በሕዝባዊ ቀመፅ መወገዳቸው ታሪካዊ ሀቅ ነው ። የባዕዳን የመረጃ መርብ በሀገራችን የቱን ያህል እንደተዘረጋ ግን ሁሉም ዜጋ ያለሀኬት እየተከታተለ ሊያከሽፈው ይገባል ።

መረጃን የመስብሰበና በተግባር የመተርጎም ጉዳይ÷ አምባገነንን ታግሎ ለመጣል ቆርጦ ለተነሳ ድርጅት ለድል መብቃት ÷ ወሳኝና ቁልፍ ጥያቄ ነው ። አሸናፊ የሚያደርጉ ምሥጢራዊ መረጃዎችን ከጠላት ጓዳ የማግኘቱ ጉዳይም እንዲህ ቀላል ባይሆንም÷ ያንን ማግኘት ግን አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ÷ ሌላ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ ሊቆጠር ይገባዋል ። የምንታገለው ጠባብ ብሄረተኛን ቡድን ብቻ ነው ። ሀገራዊው ትግል ደግሞ÷ የኢትዮጵያና የዜጎቿ ቀንደኛ ጠላት ከሆነው ከወያኔ ጋር እንጅ÷ የሚሰራውን በትክክል ሊረዳ ካለቻለውና ዝግጅትም ሆነ ፍላጎት÷ ዕውቀትም ሆነ ልምድና ጊዜ ካልነበረው ከደርግ ጋር እንዳለሆነ በመረዳት ÷ይህን መሰሪና የኢትዮጵያ ስትራተጅየዊ ጠላት በሚገባ አውቆና ተረድቶ ብቃትን ከኃይል÷ ዕውቀትን ከመሳሪያ ጋር አቅናጅቶ መታገልን የግድ ይላል ። ከዚህም በቀር÷ የተቃዋሚው ክፍል አንደነትን ፈጥሮ በኅብረት መታገል÷ ጊዜና ዕፎይታ የማይሰጥ አንገብጋቢና አጣዳፊ ሀገራዊ ጥሪ ነው ። በዕርግጥም በዚህ ጉዳይ ÷ ሁሉም ከልብ እንዲያስብበት ይገባል !

በመሆኑም÷“ **ወያኔ የትም አትደርስም** ” በሚል የሥነ ልቦና መፅናናት ÷አዕምሮን ለማባበል መጣር ተላላነት ይሆናል። የትም አይደርሱም÷ የሚለው መዘናጋት ÷ ምናልባት ለቀቢፀ - ተስፋ ጉጉት ማርኪያና ግንዛቤ ይጠቅም እንደሁ እንጅ÷አምባገነንን ለመጣል በሚደረገው ትግል ቦታ አይኖረውም። ቁርጠኝነትንም ያሳጣል። የወያኔን ማንነት÷ይዘትና ዓላማ ፤ ድርጊትና የሥራ ክንዋኔ÷በጎርይና ሥነ-ልቦናም ሆነ መስተጋብርና አቅም እንዲሁም አስተሳሰብና አመለካከት ጠንቅቆ ማወቅ የሚታገሉትን ጠላት ማንነት በትክክል የመረዳት ችሎታ እንዲኖር መሠረት ይሆናል ። በመሆኑም÷ በወያኔ ተለዋዋጭና አስመሳይ ፕሮፓንዳ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይዘናጋ እናሳስባለን ።

“ደርዘን ዲፕሎማ÷ አንድ ዲግሪ አይሆንም ” እንደተባለው ሁሉ÷ የሰላማዊ ሰልፍ ጋጋታ÷ የረሃብ አድማ ሀዘኔታ ÷ የሻማ መብራት ተማፅኖና ዋይታ ÷ ይህን ቀንደኛ ጠላት ሊያስበረግገው አልቻለም ። ምክንያቱም ÷ በሚገባው ቋንቋ አልተነገረወምና ! በሚያደማው ጎኑ አልቆሰለምና ! በሚያመው ራሱ አልተኮረኮረምና ! እኩይ ጭንቅላቱም አልተቀጠቀጠምና !

በዕርግጥ ! ተቃውሞን ፥ በሰላዊ ሰልፍ ማሰማት ፥ በረሀብ አድማ መግለፅ፥ በሻማ መብራት መማፀን፥ የሀገሪቱን መጥፋትና የሕዝቡን በደል ለዓለም ሕዝብ ማሳወቅ፥ የዲፕሎማቲክ ግል ዘርፍ ነው ። የኢትዮጵያም ሕዝብ መብትና የፖለቲካ ተግባርም ስለሆነ ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባል ። መቀጠልም ይኖርበታል። አሻፈረኝነትና አልገዛም ባይነት ሁሉ ሕዝባዊ አመፅ ስለሆነ፥ የሰላማዊ ትግል አካልና አምሳል በመሆኑ፥ የተጨቆነ ዜጋ ሁሉ ማመፁ አይቀሬ ነው። እንዲያወም፥ሊደገፍ ሊበረታታ ይገባል ። ከዚህም በቀር፥አድማሱን እያሰፋ፥ ሰልፉን እያስተካከለ ፥ ድክመቱን እያረመ ፥ ኃይሉን እያጠናከረ፥ ወዳጅ ጠላቱን እየለየ ፥ አስመሳዩን ጽሐፍ- ፈሪሳዊ ከእውነተኛው ኢትዮጵያዊ ታጋይ ለይቶ በማውጣት ፥ይህን ሰላማዊ -ሕዝባዊ አመፅ በቀጣይነት ማካሄድ አለበት ። ከዚህም በላይ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ሕዝባዊ አመፁን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ቢያካሂድ ፥ የወያኔ ዕድሜ ባጭር እንደሚቀጭ በዕርግጠኝነት መናገር ይቻላል ። የስድሳ ስድስቱ ዓም የካቲት ሕዝባዊ አመፅ ባልተጠበቀና በተፋጠነ ሁኔታ ምን ዓይነት ታሪካዊ ድል እንዳጎናፀ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኩራት ያስመዘገበው ታሪክ ነው ።

ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት “ **የዐረብ ፀደይ** ” የሚል ስያሜ የተሰጠው የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዘባዊ አመፅ ከአንድ ቦታ ተጭሮ በሚያስደንቅ ፍጥነት እንደ መንጠር አሳት በመቀጣጠል ፥ ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦችን ከአምባገነኖች አገዛዝ ነፃ እንዳወጣቸው የቅርብ ትዝታ ብቻ ሳይሆን ፥ ግለቱ እስከሁን ድረስ ፥በሥልጣን ላይ ያሉትን ሌሎች አምባገነኖችንም እያቃዠና እያባነነ ይገኛል ።

የሕዝብ አመፅ ፥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ፥ ሁሉን ባካተተ መልኩ ተቀናጅቶና ተቀነባብሮ በቀጣይነት ከተካሄደ፥ በአምባገነኖች ከርሰ-መቃብር ላይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት ወሳኝ ሚና አለው ። ስለሆነም፥ ይህ የትግል ዘርፍ በቀጣይነት መካሄድ አለበት።

የወያኔ መሪዎች፥ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም፥ዜግነታቸውን የሸጡ፥ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን የካዱ፥ታሪካቸውንና ሰብእናቸውን ያዋረዱ፥በዕለት ጥቅም፥ ዘላቂ ታሪክን የለወጡ፥የማንነት ችግር ሰለባ የሆኑ፥ኢትዮጵያዊ ኩራትና ሞገሳቸውን ለባዕዳን ጥቅም በመሸጥ ለውጭ ኃይል አደግዳጊና ሰጋጅ መሆናቸውን ያለ ሀፍረት ያስመሰከሩ ናቸው ።

ይሉኝታና ሕዝብስ ምን ይለናል የሚል ሥነ ምግባር የሌላቸውና የሰውን ልጅ ሰብዕና የሚያስከበሩ በጎርያትን ያለበሱ በመሆናችው፥ ከሀገሪቱ ጋር ተለያይተው ከታሪክ ጋር ተጣልተው፥ ከሕዝቡ ጋር ተቆራርጠው ይኖራሉ። በመሆኑም ነፃ እናወጣዋለን የሚሉትን የትግራይን ሕዝብ እንኳን ሳይቀር አሳዝነውታል ። ይህ ሁኔታ፥ የሥነ-አዕምሮ ተቅበዝባዥ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ። ዛሬ፥ የትግራይ ሕዝብ፥ወያኔን “ **ከአንተ የሚመጣው ልማትና ዕድገት ባፍንጫችን ይውጣ እንጅ፥ ከወገናችን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ግን መቆራረጥ አንፈልግምና አታለያየን ! ብትሞክርም፥ እኛ አንለያይም ።** ” እያለው ይገኛል ። ይህ የአርቆ አስተዋይ አባባል ፥ የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት ከሚሰማው ዜጋ ሁሉ የሚጠበቅ በመሆኑ ፥ ለነገዋ ኢትዮጵያ አንድነት ፥ የጋራ ዕድገትና ብልፅግና ለሚጫወተው ሚና መሠረት ይሆናል ብሎ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያምናል ። ዘላቂ አንድነትና የጋራ ጥቅም የሚመጣውም፥ በዘርና በቋንቋ ተለያይቶ በሚከናወን የቡድን ሀብትና ጥሪት ማግበስበስ ሳይሆን ፥ በአድነትና በእኩልነት ላይ በተመሰረተ ሁሉንም ዜጋ የሚጠቅም የዕድገት ጉዳና ብቻ ነው ። የወያኔ መሪዎች ግን “ **ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋልና ሞኝ አሳላፊ ዘመዱ አይጠቅምም** ” የሚል ኋላ -ቀር ይትብኃልን በመጠቀም፥ በዕለት ፍርፋሪ ላይ አተኩረዋል። ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ፥ በትውልድና በታሪክ ዘንድ የሚያስወቅስና የሚያስጠይቅም አሳፋሪ ወንጀል ይፈፅማሉ ።

ኢሕአፓ፥ “ **ብኩሩናውን፥ በጭብጥ ምስር** ” በመለወጥ፥በሀገርንና በሕዝብ ጥቅም ላይ

ያልተደራደረና የማይደራደርም በመሆኑ፥ ኢትዮጵያዊ ዓላማው ግቡን አይስትም ፡፡ ይህ፥ ጊዜ የማይሽረውና ወቅታዊ የፖለቲካ ችርቻሬ የማይለውጠውን መሠረታዊ ባኅርይ ፥ የሚታገልለት ሕዝብ በሚገባ ተረድቶለታል ፡፡ በመሆኑም በሕዝቡ ዘንድ፥ " ኢሕአፓ ምን አለ ? " የሚል ሕዝባዊ አመኔታን አትርፎለታል ፡፡ ይህም በበኩሉ፥ ለፓርቲ አባላት የትግላቸው ፅናት የአንድነታቸው ብርታት ፥ የዜግነታቸው ኩራት ሆኗቸዋል ፡፡ ይህ ሰብዕናው፥ ባላንጣዎቹና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች " አክራሪ " የሚል ስም ሊሰጡት ይከጅላሉ ፡፡ በዓላማ ፀንቶ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም በአይበገሬነት መታገል፥ አክራሪነት ከሆነ ፥ እስየው ከማለት የተሻለ መልስ አይኖርም ፡፡ በየጊዜው በሚለዋወጡ ሁኔታዎች ምክንያት መሠረታዊ ዕምነትን መቀያየር፥ የፖለቲካ ድግስ ወጥ ቀማሾች ባኅርይ እንጅ ኢሕአፓን ሲያልፍም አይነካው ፡፡

" ከስቶ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ " ሆኖ ነው መሰል፥ የትግል ፅናት፥ እንደ ጅማት የከረረ ይመስላቸዋል ፡፡ እነ ኔልሰን ማንዴላ እኮ ዘረኛውን የአፓርታይ ሥርዓት ሊደመስሱ የበቁት ከሰባ ዓመት በላይ በአይበገሬነት ታግለውና ተሰቃይተው ፥ አይከፍሉ መሥዋዕትም ከፈለው ነው ፡፡ አንድ የኢሕአፓ ታጋይ፥ " የትግሉ ነው ሕይወቴ ! " ብሎ ቃል የገባው ፥ ለመፌክር ማጣፈጫ ፥ ለመዝሙር ማድመቂያ ፥ ለሰላመዊ ሰልፍ ማቀንቀኛ ፥ ብሎ አይደለም ፡፡ ለፅኑ ዓላማው መግለጫ እንጅ !

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ፥ ከታሪኩ ጋር አቆራኝቶ ፥ከባኅሉ ጋር አዛምዶ ፥ ከዕምነቱ ጋር አዋህዶ አክብሮና ጠብቆ ያቆያቸው የሥነ-ምግባር ዕሴቶች፥የራሱ አንጡራ ንብረቱና የማንነቱ መግለጫዎች በመሆናቸው መሠረታቸው የማይናወጥ፥ ምሶሷቸው የማይናጋ ፥ ግድግዳቸው የማይነቃ ነው ፡፡ ይህም በመሆኑ፥ የርዕዮተ-ዓለም ምንዛሬዎች፥ የፖለቲካ መሪዎች ብወዛዎች ሊሆኑ አይችሉም ፡፡ ይህንም፥ ቅጥ-አባሩ ጠፍቶበት የነበረው ደርግም ሞክሮ እንዳልተሳካለት ሁሉ ፥ ወያኔዎቹም የሚሳካላቸው አልሆነም ፡፡ አይሆንምም !

ጠላቶቿ፥ወደዱትም ጠሉቱ ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን በዕምነት፥ በታሪክና በባኅል የዳበረችና የበለፀገች ሀገር ናት፡፡ ሦስቱም ታላላቅ ሃይማኖቶች፥ ማለትም፥ ኦሪት፥ ክርስትናና እስላምና የሀገሪቱ ነባርና ጥንታውያን የዜጎቿ ዕምነቶችና ቅርሶች ሆነው ቆይተዋል ፡፡ ምዕመናኑም፥ በየዕምነታቸውና አምልኳቸው ፥ተከባብረው ተፈቃቅደውና ተባብረው ለዘመናት አብረው ኖረዋል ፡፡ ደስታንና ሀዘንን፥ መከራና ፀጋን፥ የተፈጥሮ አደጋዎችንም ሆኑ፥ ሰው-ሰራሽ ችግሮችን በጋራ ተካፍለውል ፡፡የውጭ ወራሪ ኃይሎችንና የውስጥ አምባገነኖችንም በጋራ አስወግደዋል፡፡ ይህ ሁሉ የአንደነታቸው ፅናት ቀጥታ ነፀብራቅ ሆኖ ኖሯል ፡፡ ወደ ፊትም ይኖራል ፡፡ይህንን የፀና አድነትና ትብብር፥ ለማናዎጥ በየጊዜው ብዙ ሙከራዎች ተደርገው ነበር ፡፡ በየጊዜው አያሌ ጥረቶች ቢሞከሩም ሁሉንም በመተባባር እንዳመጣጣቸው አክሽፈዋቸዋል ፡፡ ለዚህም ነው፥ ወያኔ ለአለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሄርና በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት፥ እንዲሁም በሌሎች ጥቃቅን ልዩነቶች በመከፋፈል ፥ እርስ በእርስ ለማፈጀት ያደረገውና የሚያደርገው እኩይ ተግባር ሊሳካ ያልቻለው ፡፡

በአንዳንድ አካባቢ ሆን ተብሎ ሕዝብን ለማፈጀት በተደረገው የወያኔ መሰሪ ተንኮል ምክንያት፥ትውልድና ታሪክ በማይረሳው ወንጀል ቁጥራቸው በትክክል ያለተመዘገበ የንፁሃን ዜጎች ደም በከንቱ ቢፈስም፥ የዚህ ብሄራዊ ወንጀል ተጠያቂ ወያኔና የወንጀሉ ተባባሪዎች እንጅ ብሄር-ብሄረ-ሰቦች ሊሆኑ አይችሉም ፡፡ ለዚህም ነው፥ የወያኔ መሪዎች " እኛ በሥልጣናችን ከሌለን፥ ሊፈጁህ አድፍጠው የሚመጠባበቁ አሉ ! ለራስህ ህይወት ስትል እኛን እየደገፍ መኖር አለብህ " በማለት የዕድሜያቸው መቀጠያ የሚሆን መሰሪ ፕሮፓጋንዳ የሚነዙት ፡፡ ይህንን ቢያድረጉ ግን አይፈረድባቸው ፡፡ ምክንያቱም ነግ- ከነገ ወዲያ የሚጠብቃቸውን የሕዝብ ፍርድ ያውቁታልና !

የወያኔ ጠባብ ብሄረተኛና ዘረኛ ስብስቦች፥ በኢትዮጵያና በዜጎቿ ላይ የፈፀሙትን ወንጀል መመዝገብ የተገባ ነው። በዚህ ታሪክና ትውልድ በማይረሳው ብሄራዊ ወንጀል ምክንያት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የደም እምባ እያነባ ይገኛል ። በደረሰበት ብሄራዊ ጥቃት፥ በደል ፥ ውርደትና ሀፍረት የተነሳም ፥ አንገቱን ደፍቷል ። ከሀገራዊ ጥቃትና በደል ለመወጣት የሚያበቃውን ጊዜ በጉጉት ይጠብቃል ። ምናልባትም የዛሬው ዕምባ ፅዋው ሞልቶ ሲገነፍል ፥ ነገ ወደ ደም ገንዳ ሊለወጥ የማይችልበት ሁኔታ አይመጣም ለማለት ያስቸግር ይሆናል። “ በደም የኖሩ በደም ይጠፋሉ ” ከተባለው አባባል፥ ወያኔዎቹና የወንጀላቸው ተባባሪዎች ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት አይቻልምም ይሆናል ። ነገር ግን ፥ የወቅቱ ትውልድ ተግቶ መስራት የሚገባው፥ የኢትዮጵያን የኳኅለ ቁስሏን ለመጠገን እንጅ የረዥም ዘመን ሰቆቃዋን ለማስቀጠል ከቶ ሊሆን አይገባም የሚል የፀና ዕምነት አለን ።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ኅብረት ሰብ፥ የዘንድሮውን የግንቦት አንድ ቀን በዓሉን በነፃነት ሊያከብር አለቻለም ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሀገሩ፥ በአንድ ዘረኛ ሥርዓት አምባገነን ቡድን ስር በመውደቋ ምክንያት፥ የዴሞክራሲ ጭላንጭል የማይታይባት በመሆኑ ነው ። ይህንንም ሀቅ መላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች በሚገባ ይረዱታል። ያላቸው አንድ ምርጫ እንደሆነም የገነዘባሉ ። ለመፃዒ ዕድላቸው ብሩኅ ተስፋ፥ ዛሬ ከመላው የሀገሪቱ ዜጋ ጋር በመሆን ይህን ጨቋኝ ሥርዓት ለማሰወገድ መቻል እንደሆነ ያውቁታል ። የሀገርና የሕዝብ ጠላት የሆነን አምባገነን ሥርዓት ለመጣል ፥ማነኛው ዜጋ ሁሉ መተባበር እንዳለበት የኢትዮጵያ ሠረተኞች ማኅበር ከየካቲት 1966 ዓም ያገኙት በቂ ተመክሮ አላቸው። ሕዝባዊ አመፁን በሀገረ አቀፍ ደረጃ አስተባብሮ ለመታገል በሚደረገው የትግል ሂደት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ወሳኝ ሚና ስለሚኖረው፥ እንደ የካቲቱ ስድሳ ስድስት ሕዝባዊ አመፅ ተባብሮ እንዲነሳ፥ኢሕአፓ ሀገራዊ ጥሪውን የስተላልፋል !

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጥላል !
ኢትዮጵያ በነፃነት ትኖራለች !